


እንደምን ከርማችኋል የቅዳሜ ገበያ አንባቢያን? የዛሬው ጽሁፌ መነሻና መድረሻ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ቤት ሲገዙ የሚያገኟቸው ጥቅሞችና ጥንቃቄ ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በሚመለከት ይሆናል። በሃገራችን የቤቶች ግብይት ውስጥ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተሻለ ተጠቃሚ የሚያደርጓቸው በርካታ ሁኔታዎች በመኖራቸው የተነሳ በግብይቱ ዋና ተዋናይ ሆነው ይታያሉ።

## ቤት በሀገር ቤት ሲገዙ ያሏቸው ጥቅሞች

ሀ) ከሀገራቸው ጋር ያላቸው ትስስር ይጨምራል፤

ለ) በሀገራቸው ቋሚ ንብረት አፍርተው ቤተሰቦቻቸውን ለመጦር ይችላሉ። ለእነሱም የማረፊያና በጡረታ ወቅት መጠቀሚያ ይሆናቸዋል፤

ሐ) በዲያስፖራ ፋይናንሲስግ ለቤት መግዢያ እስከ አስር በመቶ ድረስ ብቻ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው ቀሪውን 90% ብድር ከባንኮች ለማግኘት መቻላቸው፤

መ) በተመረጡ ቦታዎች ላይ በተጠና መንገድ ቤቶችን በመግዛትና የቤት ቁስ በሟሟላት በጥሩ ዋጋ በማከራየት ጥሩ ገቢ ያገኙበታል፤

ሠ) በተከፋፈለ የአከፋፈል ሁኔታ በብር በሚደረግ ክፍያ ውል ገብተው ከሚገነቡ ሪል እስቴት አልሚዎች ሲገዙ በየእለቱ ከሚወርደው የብር ምንዛሪ ተጠቃሚ ይሆናሉ። በውጭ ምንዛሪ ስሌት በብር የሚከፈል ግብይት ውስጥም ተጠቃሚነታቸው ላቅ ያለ ነው፤

ረ) እንደ ኢንቨስትመንት ለሚያስቡትም ከርቀት ሆኖ የሚሰራ ቀላል እና አዋጭ የስራ ዘርፍ ነው። ዛሬ የተገዛ ቤት ከሁለትን ከአራት አመታት በኋላ ጥቂት እየተጨመረበት አራትና አምስት እየሆነ ሊበዛ የሚችል ነው።

## ሊጠነቀቁባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

ሀ) ገበያውን በደንብ ማትናት፤ ብዙ አማራጮች ስላሉ ከመወሰንዎ በፊት በርካታ አማራጮችን እንዲመለከቱና ጥቅሞችዎን አስልተው አቅምዎትን አይተውና ገምግመው እንዲገዙ ይመከራል፤

ለ) የግብይት ባለሙያዎችን መጠቀም፤ በተለይም በሪል እስቴት ዘርፍ ግብይት ውስጥ ጥሩ ሙያና እውቀት ያላቸውን የግብይት ባለሙያዎችን እገዛና ምክር መጠቀም ያስፈልጋል፤

ሐ) ህጋዊ ጉዳዮችን መለየት፤ የሪል እስቴት ግብይት ከፍ ያለ ነዋይ የሚፈስበት በመሆኑና በሀገራችን ወጥ የሆነ የግብይት መመሪያ ስለሌለ፤ እንዲሁም በተለያዩ አልሚዎች የሚዘጋጁ የግብይት ውሎች ብዙ ልዩነት ስላላቸው የግብይቱን ሂደት እና የሚዋዋሉትን ውል በህግ አማካሪ ወይም በግብይት ልምድ ባለው የማርኬቲንግ አማካሪ እንዲጠቀሙ ይመከራል፤

መ) የፋይናንስ አማራጮችን መለየት፤ ገዢዎች ቤት ከመግዛታቸው በፊት ግብይቱ የሚጠይቀውን ክፍያ በሚፈለገው ጊዜ ሊያገኙበት የሚችሉት እና የተሻሉ የባንክ ብድር እና ከክፍያ ጋር የተያያዙ ቅናሾችን ለይቶ መጠቀምን ታሳቢ ያድርጉ፤

ሠ) ጉብኝት ማድረግ፤ የሚገዙትን ቤት ውሳኔ ከመወሰንዎ በፊት ጊዜዎትን አተካክለው ወደ ሀገርቤት መጥተው በአካል አማራጮችን፤ ቤቶቹ የሚገኙበትን አካባቢም ቢመለከቱ ካልታሰበ ኪሳራ ይተርፋሉ፤

ረ) መሰረተ ልማትን መመልከት፤ ቤት ብቻውን ቢያምር ዲዛይኑም ማራኪ ቢሆን ግንባታውም ቢጠናቀቅ መሰረተልማት ካልተሟላለት የታለመለትን የመኖሪዬነትም ሆነ የኢንቭስትመንት ዓላማ ስለማያሳካ መሰረተ ልማቱ መሟላት አለመሟላቱን፤ ለማሟላት ቀላል ወይም ከባድ መሆኑን ተስፋውንም መገምገም ይገባል።

## ማጠቃለያ

ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከርቀት ሆነው ለሚያደርጉት የቤት ግብይት ትኩረት ሰጥተው፣ በባለሙያ ታግዘው፣ ጥቅማቸውን አስልተው፣ አማራጮችን ተመልክተው አመዛዝነው፣ መርጠው፣ የግብይት ውሎችን መርምረው፣ አስቻይ የአከፋፈል ስርዓቶችን ለይተው ቢሆን ይመከራል።

የተቋማችን አንድ አካል የሆነው አቡቀለምሲስ የሪል እስቴት ገበያ Abukelemsis Real Estate Market and Consultancy ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቤት ገዢዎችን ከየትኛውም ዓለም ቢገዙ #ነጻ_የማማከር አገልግሎት ይሰጣል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት በሚከተለው አድራሻ ሊያገኙን የችላሉ።

Website: www.abukmarketing.abukgroup.com
Email: deskebede@gmail.com